የሰበር መ/ቁ 265878

ጥቅምት 5 ቀን 2018 ዓ/ም

T05G

ዳኞች - ቴዎድሮስ ምህረት

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

ተሾመ ሽፈራው

ብርቅነሽ እሱባለዉ

ሀፊዝ አባጀማል

አመልካች --- መጋቤ ጥበብ ፅጌ ቅባቱ ተስፋ ማርያም

ተጠሪዎች --- 1. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

2. የደብረ ምጥማቅ ሰአሊተ ምህረት ቅ/ማርያምና ቅ/ክርስቶስ ሰምራ ካቴድራል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ችሎት ውሳኔ ይሻል የተባለው ጉዳይ የሥራ ክርክር ችሎት የአሁን አመልካች በስራ ቦታየ ተመልሸ ተመድቤ እንድሰራ እና ለቦታው (ለዋና ሂሳብ ሹምነት የሥራ ደረጃ) የሚገባውን ክፍያ ተጠሪዎች እንዲከፍሉኝ ይወሰነልኝ በማለት ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ፍርድ ቤቱ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት የመወሰኑን ህጋዊነት የሚመለከት ነው።

1. ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ሥራ ክርክር ችሎት ባቀረቡት ክስ አሰሪያቸው የሆነው ያሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ አዛውሮ የማሰራት መብት ቢኖረውም ከህግ ውጪ የሥራ ደረጃየን ዝቅ በማድረግ በ2ኛ ተጠሪ እንድሰራ የፈፀመው ምደባ ህገወጥ ነው ተብሎ ለዋና ሂሳብ ሹምነት የሥራ ደረጃ የሚከፈለው ተጨማሪ የአበል ክፍያና ጥቅማጥቅም እንዲከፈለኝ፤ የቤተክርስቲያኒቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ በሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሰረት እና 1ኛ ተጠሪም ደረጃየ ተጠብቆ በዋና ሂሳብ ሹምነት የሥራ መደብ ላይ እንደምመደብ ሰኔ 26/2015 ዓ.ም እና ታህሳስ 24/2016 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ባረጋገጠልኝ መሰረት በሥራ ቦታየ አየር ጤና አንቀጸ ብርሃን ቅድስት ኪዳነ ምህረት ካቴድራል በዋና ሂሳብ ሹምነት የሥራ መደብ ላይ መልሶ (መድቦ) እንዲያሰራኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

2. ተጠሪዎች ለክሱ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካች ክስ ያቀረቡት የቅዱስ ሲኖዶሱን ዉሳኔ መሰረት በማድረግ ሲሆን ይህ የቅዱስ ሲኖዶስ ዉሳኔ በአስተዳደራዊ ጉባኤ የአፈፃጸም ሂደት ታይቶ የሚያልቅ ጉዳይ እንጅ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀረብ ጉዳይ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት ተከራክረዋል። በፍሬ ጉዳዩም ዝርዝር መልሳቸዉን አቅርበዋል።

3. የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ሥልጣን ያለው ስለመሆን አለመሆኑ መርምሮ ብይን ሰጥቷል። በሰጠው ብይን የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 234706 በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የሲኖዶስ አስተዳደራዊ ውሳኔን የሚመለከት ከሆነ ጠያቂው አስተዳደራዊ ስርዓት ተከትሎ ከሚጠይቅ በስተቀር ጉዳዩ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት ሥርዓት አለመኖሩን ወስኗል፤ ስለሆነም በዚህ የሰበር ውሳኔ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 9 እና 231(1)(ለ) መሰረት ፍርድ ቤቱ ከሳሽ ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው ስልጣን የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል። አመልካች ይህን በመቃወም ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት በመሰረዝ ውሳኔ ተሰጥቷል።

4. የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች ሰኔ 5/2016 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ እና የሰበር አጣሪ ችሎቱ ጉዳዩን የመራበት ትዕዛዝ ተመርምሮ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን የለዉም በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ብይን በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመፅናቱን አግባብነት ከአመልካች ክስ ይዘት እንዲሁም የስር ፍርድ ቤቶች ለብይኑ መሰረት ካደረጉት በሰ/መ/ቁ 234706 ከተሰጠዉ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ግራቀኙ መልስ እና የመ/መልስ ተለዋውጠዋል።

5. የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 234706 ጥቅምት 5/2016 ዓ.ም በተመሳሳይ ክርክር በሰጠው ውሳኔ "በሲኖዶስ ትዕዛዝ መሰረት እንደ ተጠሪዎች ያሉ አካላት ካልፈጸሙ ባላቸዉ አሠራር መሰረት በአስተዳደር ረገድ እንዲፈጽሙ ከሚደረግ በቀር ተጠሪዎች በፍርድ ተገደዉ ውዝፍ ክፍያ እንዲፈጽሙ፣ ..... የሚወሰንበት አግባብ የለም፤ የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ መሰረት አድርጎ በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 9(1) እና 231(1/ለ) መሰረት መዝገቡን መዝጋት አለበት" በማለት ውሳኔ መስጠቱን ተገንዝበናል።

6. ይህ የሰበር ትርጉም በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ ማግኘት ህገመንግስታዊ መብት ስለመሆኑ ከሚደነግገው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1)፤ በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ በቀር ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ክስ ተቀብለው ለማከራከር ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ ከሚደነግገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4 ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተቀብሎ ለማየት እና ለመወሰን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139(1) ስር ከተሰጠው የስራ ክርክር የዳኝነት ሥልጣን፤ እንዲሁም የሀይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሰርቱት የስራ ግንኙነት ላይ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚኖረውን ተፈፃሚነት በተመለከተ ከወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 342/2007 አንጻር ተገቢ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ የተያዘውን ጉዳይ መወሰን ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ከአምስት በላይ በሆኑ ዳኞች ሊታይ ይገባል ተብሎ የሰባት ዳኞች ፓናል ችሎት እንዲሰየም ተደርጓል።

7. እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች የቀረበውን ክስ ተቀብሎ በማየት አከራክሮ ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን የለኝም የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው አመልካች በክሳቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቋሚ ሲኖዶስ ደመወዜ እና ጥቅማጥቅሜ ተጠብቆ መድበው እንዲያሰሩኝ በወሰነው መሰረት ተከሳሾች ደመወዜን እና ጥቅማጥቅሜን ጠብቀው መድበው እንዲያሰሩኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን ካቀረቡት አቤቱታ እና የሰነድ ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል፤ ፍርድ ቤቱ በከሳሽና ተከሳሾች መካከል ባለው የስራ ውል ግንኙነት መሰረት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት በተዘረጋው ስርዓት አግባብ ግንኙነታቸውን በማየት ተከሳሾችን ከማስገደድ ባለፈ በሲኖዶሱ ውሳኔ መሰረት እንዲፈፀም ለማለት ወይም ለማስገደድ የሚያስችለው የስረ ነገር ሥልጣን የለውም፤ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 234706 በተመሳሳይ ጉዳይ በሰጠው ትርጉምም ከሳሽ አስተዳደራዊ ስርዓት ተከትለው ከሚጠይቁ በቀር በፍርድ ቤት የሚታይበት ስርዓት አለመኖሩን ወስኗል፤ ስለሆነም በሰበር ውሳኔው እና በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 9(1) እና 231(1/ለ) መሰረት ፍርድ ቤቱ አመልካች ያቀረቡትን ክስ አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው ስልጣን የለውም በማለት ነው፡፡

8. አመልካች ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ተጠሪዎች የስራ ደረጃዬን ጠብቀውና መድበው እንዲያሰሩኝ እንዲወሰንልኝ የዳኝነት ጥያቄ ባቀረብኩበት ሁኔታ አመልካች ሲኖዶሱ የሰጠውን ውሳኔ ያስፈጽምልኝ የሚል የዳኝነት ጥያቄ እንዳቀረብኩ ተደርጎና ሰበር ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ባልተገባ መንገድ ተተርጉሞ ፍርድ ቤት የስራ ክርክሩን ለማየት ስልጣን የለውም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሮ አመልካች እንደ ክስ አቀራረቤ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

9. ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ቅዱስ ሲኖዶስ የካቲት 29/2015 ዓ.ም እና ጥቅምት 30/2016 ዓ.ም ባደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ያስተላለፈውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለንም በማለት ያሳለፉት ብይንና ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ሊፀና ይገባል፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተክርስቲያኑ የባይ አካል እንደመሆኑ መጠን የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በሕገ-ቤተክርስቲያኒቱ ሕገ-ደንብ አንቀጽ 12 እና በቃለ-አዋዲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ትርጉም ሰጥቶ በአስተዳደር በኩል ታይቶ የሚፈፀም እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ሊታይና አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሊሰጥበት የማይገባ በመሆኑ በሰበር መ/ቁ 234706 ጥቅምት 5 ቀን 2016 በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤቶች ታይቶ ሊወሰን አይገባውም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

10. እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የመጨረሻው ከፍተኛው የስልጣን ባለቤት በሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠን ውሳኔ ፍርድ ቤቶች በአለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ህግ መሰረት አይተው ትክክል ነው አይደለም በማለት ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት ስልጣን የላቸውም፡፡ ከዚህም ሌላ ቤተክርስቲያኗ ከቅዱስ ሲኖዶስ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲን ከላይ ወደታች የሚወርድ መዋቅር ያላት መሆኑ የሚያከራክር ባለመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛው የስልጣን ባለቤት እንደመሆኑ መጠን የሚሰጠውን ውሳኔ ከቅዱስ ሲኖዶስ በታች ያሉት መዋቅሮች ሊያከብሩት የሚገባና ተፈፃሚነት ያለው መሆኑም ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡

11. ይሁንና የስራ ክርክር እንዲወሰን ከተጠየቀው የዳኝነት ጥያቄ አንጻር በተጠሪዎች እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መካከል ሊኖር የሚችል ከቤተክርስቲያኗ የውስጥ አስተዳደር ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው በማለት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ታይቶ ሊወሰን የሚችልን የስራ ክርክር ጉዳይ ፍርድ ቤቶች ተቀብለው በማከራከር ውሳኔ እንዳይሰጡ ምክንያት ሊሆን የሚችል መሆን አለመሆኑን በማጣራት አስቀድሞ በሰበር ችሎት ተሰጠ የተባለው ትርጉም ሊለወጥ የሚገባ መሆን አለመሆኑ፤ እንዲሁም የሥር ፍርድ ቤቶች በተያዘው ጉዳይ የዳኝነት ስልጣን የለንም በማለት በደረሱበት መደምደሚያ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል።

12. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ሥር ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል። በሌላም በኩል የፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርሆች አንዱ የመንግስት እና ኃይማኖትን መለያየትን የተመለከተ ሲሆን መንግስትና ኃይማኖት የተለያዩ መሆናቸው፤ መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ፤ ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 11(1) እና (3) ተመልክቷል።

13. በአንፃሩ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ በቀር የፍትሐብሔር ክስ ተቀብለው ለማከራከር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4 ይደነግጋል። የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 80202 እና በሌሎች ተመሳሳይ መዝገብት ላይ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው አስከሆነ ጉዳዩን ለማየት በህግ በግልጽ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ሌላ አካል አስከሌለ ድረስ ጉዳዩ በቀጥታ በፍ/ቤት ቀርቦ ሊስተናገድና ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችልና የሚገባ ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል።

14. የስራ ክርክሮች የሚዳኙበትን አግባብ እና የዳኝነት ስልጣን በተመለከተ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የሥራ ክርክር እንደ የጉዳዩ ዓይነት እና ባህርይ ለአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ወይም ለሥራ ክርክር ችሎት ሊቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን የትኛዉ ዓይነት ጉዳይ ለየትኛዉ የዳኝነት አካል እንደሚቀርብ በግልጽ ለይቶ አስቀምጧል። የአዋጁ አንቀጽ 139 በፍርድ ቤት ሊታዩ ስለሚችሉ የስራ ክርክሮች የሚደነግግ ሲሆን፣ የአዋጁ አንቀጽ 143 (1) (ለ) እስከ ( ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 147 አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ስልጣንን ይደነግጋሉ።

15. በተያዘዉ ጉዳይ የክሱ ምክንያትና የተጠየቀው ዳኝነት 1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ አዛውሮ የማሰራት መብት ቢኖረውም ከህግ ውጪ የሥራ ደረጃየን ዝቅ በማድረግ በ2ኛ ተጠሪ እንድሰራ የፈፀመው ምደባ ህገወጥ ነው ተብሎ ለዋና ሂሳብ ሹምነት የሥራ ደረጃ የሚከፈለው ተጨማሪ የአበል ክፍያና ጥቅማጥቅም እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል በመሆኑ ክሱ ወደሌላ ቤተክርስቲያን የተደረገ ዝውውርን እና ከዚህ ጋር በተያያዘ የተነሳ የደመወዝ እና አበል ክፍያዎችን የሚመለከት ነው። በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ ለሚሸፈን ሰራተኛ ከዝውውር ጋር የተያያዙ ክርክሮች የመወሰንን ስልጣን በተመለከተ ጉዳዩ ለፍርድ ቤትም ሆነ ለቦርድ ሊቀርቡ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 በአንቀጽ 139(1/ሠ) ፣ በ143 (1/ሰ) እና 147 (1/ለ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች

መገንዘብ ይቻላል። ዝውውርን መነሻ ያደረገ ዳኝነት ለቦርድ ሊቀርብ የሚችለዉ ክርክሩ የወል ባህርይ ሲኖረዉ ብቻ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ በ 143 (1/ሰ) እና 148 (1/ለ) ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፤ በሌላ በኩል ለፍርድ ቤት የሚቀርበዉ ግን ክርክሩ የግል ባህርይ ሲኖረዉ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 139 (1) ያስረዳል። በእርግጥ አዋጁ የወል የሥራ ክርክርን አስመልክቶ የሰጠዉ ትርጉም የለም። ይሁንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 18180 አንድን ክርክር የወል ወይም የግል ብሎ በመወሰን ረገድ ግምት ዉስጥ ሊገቡ የሚገባቸዉን መስፈርቶችን አስመልክቶ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል። በዚህ ትርጉም መሰረት ክርክሩ የወል ለመባል የጋራ የሆነውን የሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚመለከት ሊሆን እንደሚገባ እና የወል የሚሰኘዉም ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ዉጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ። በአንፃሩ ክርክሩ የግል ነዉ የሚባለዉ ዉጤቱ በሠራተኛዉ መብት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሲሆን ነዉ። ስለሆነም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የግል የስራ ክርክርን የተመለከተ ነው ብለናል።

16. ሌላው መታየት ያለበት ነጥብ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን ነው። የሐይማኖት ወይም የበጎ አግራጎት ድርጅቶች በሚመሰርቱት የስራ ግንኙነት ላይ አዋጁ ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚንስትሮች ምክር ቤት በደንብ ሊወስን እንደሚችል በህጉ ተደንግጓል። በመሆኑም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጁ የሃይማኖት ተቋማት በሚመሰርቱት የስራ ግንኙነት ላይ የሚኖረውን ተፈፃሚነት የሚወስነው የሚንስትሮች ም/ቤት ደንብ ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክርን የተመለከተ ክስ ተቀብለው አከራክረው እንዳይወስኑ በቀጥታ ወይም በግልጽ ያደረገው እገዳ ካለ ሊታይ ይገባል።

17. ከፍሲል እንደጸመለከታ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 3(3)(ለ) መሰረት የሐይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሰርቱት የስራ ግንኙነት ላይ አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚኒስትሮች ም/ቤት በደንብ ሊወስን እንደሚችል በግልጽ ተደንግጓል። የሚኒስትሮች ም/ቤት የተጠቀሱትን ተቋማት በተመለከተ ደንብ ቁጥር 342/2007 አውጥቷል። በእርግጥ ይህ ደንብ የወጣው አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት አድርጎ ሲሆን የዚህን አዋጅ መሻር ተከትሎ የደንቡ ተፈፃሚነት ላይ የሚኖረው ውጤት መታየት አለበት። በሁለቱ አዋጆች ተመሳሳይ ድንጋጌ የሆነው አንቀጽ 3(3)(ለ) የይዘትም ሆነ የቃላት ለውጥ ሳይደረግበት የቀጠለ ነው። ጥያቄ የሚሆነው የእናት አዋጁ (Parent act) መሻር አዋጁን መሰረት አድርገው የወጡ ተከታይ ህጎች (subordinate legislation) ላይ የሚኖረው ዉጤት ምንድ ነው የሚል ነው። ከዚህ አንፃር ተቀባይነት ያለው አጠቃላይ መርህ በዋናው ህግ በግልጽ እስካልተሻሩና ዋናውን ሕግ እስካልተቃረኑ ድረስ በዋናው ህግ ስር የወጡ ደንብ እና መመሪያ ተፈፃሚነት እንደሚቀጥል ነው። የአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 192(2) ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ውሳኔዎች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደሌቸው ደንግጓል። ይህ ድንጋጌ ቢኖርም የአዋጁ አንቀጽ 190(1) አስቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የወጡ ደንብና መመሪያዎች ከአዋጁ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነታቸው እንደሚቀጥል ተመልክቷል። ደንብ ቁጥር 342/2007 የአዋጁን አንቀጽ 3(3)(ለ) ተፈፃሚ ለማድረግ የወጣ ሲሆን ድንጋጌው ከፍሲል እንደተጠቀሰው

በሁለቱም አዋጆች ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ በአዲሱ አዋጅ ስላልተሸረና ከአዋጁም ስለማይቃረን ደንቡ ተፈፃሚ የማይሆንበት የህግ ምክንያት የለም።

18. የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 342/2007 አንቀጽ 3 ስር በሐይማኖት ድርጅቶች መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ አገልጋዮች ላይ አዋጁ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው፤ በአንፃሩ አስተዳደራዊ እና የበጎ አድራጎት ተግባርን ለማከናወን በተሰማሩ ሰራተኞች ላይ አዋጁ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ተመልክቷል። የደንቡ አንቀጽ 2(1) "መንፈሳዊ አገልግሎት" ማለት በሃይማኖት ድርጅት ውስጥ ከእምነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን መንፈሳዊ ተግባራትን ብቻ ማከናወን እንደሆነ ትርጉም ሰጥቶበታል። የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 18419 ላይ በሃይማኖት ተቋም ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚሸፈን ስላለመሆኑ እና በሃይማኖት ተቋም ውስጥ እንደ የሂሳብ ሰራተኛ፣ የንብረት ሰራተኛ የሆኑት ደግሞ እንደ መንፈሳዊ አግልግሎት እንደማይቆጠሩ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል።

19. ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚከራከሩበት ዋና ሂሳብ ሹምነት የስራ መደብ አስተዳደራዊ ተብሎ ሊገለጽ የሚችል ሲሆን የዳኝነት ጥያቄውም የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው። ጉዳዩም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጁ የሚሸፈን ነው። ከፍሲል ከተመለከቱት የህጉ ድንጋጌዎች እና የሰበር ውሳኔዎች መረዳት የሚቻለው አመልካች ያቀረቡትን የስራ ክርክር ተቀብሎ በማየት ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት ስልጣን ያለው ከፍርድ ቤት ውጪ ሌላ አካል ስለመኖሩ በህጉ አልተመለከተም። ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ፍርድ ቤቶች ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ እና የስራ ክርክሮችን ለመወሰን በህግ የተዘረጋውን ስርዓት በጥብቅ ተከትሎ መወሰን ይገባል።

20. አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት በ1ኛ ተጠሪ ተፈጽሟል ያሉትን ዝዉዉር የሚመለከት እና በዚህ ምክንያት አጣሁት ያሉትን የደመወዝ እና የተለያየ አበል ክፍያዎችን ሚመለከት በመሆኑ በክርክሩ ሂደት የሚታየዉ 1ኛ ተጠሪ አመልካችን ያዘዋወረው በተገቢው አግባብ ነው አይደለም? በዚሁ ምክንያት ተጠሪ ያለአግባብ ተቀነሰብኝ ያሉትን ደመወዝና የተለያዩ አበሎች ሊከፈሏቸው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን የሚመለከት ነው።

21. ይህ ደግሞ የግራቀኙን ክርክር እና የዝውውሩን ምክንያቶች በመመርመር ታይቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት ሲሆን፣ ዉጤቱም ከአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ዉጪ የሲኖዶሱን ውሳኔ ተገቢነትና አፈፃፀም የሚመለከት አይደለም። መሰል ጉዳዩች ከሌሎች ሰራተኞች ጋር በሲኖዶሱ ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተደርጎ ነበር በሚል አመልካች በክስ አቤቱታቸው መጥቀሳቸው የዳኝነት ጥያቄያቸውን ለማጠናከር የቀረበ ከሚሆን በቀር የፍርድ ቤቱን የስራ ክርክር ችሎት በህግ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ቀሪ ሊያደርግ የሚችል አይደለም። ከፍሲል እንደተገለፀው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ ማግኘት ህገመንግስታዊ መብት ሲሆን ፍርድ ቤቶችም በህጉ በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ በቀር ክስ ተቀብለው ለማከራከርና ለመወሰን ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ የዳኝነት ጥያቄዎችን ህግ ከሚደነግገው ውጪ ሥልጣን የለንም በሚል ውድቅ ማድረግ ተቀባይነት የለውም።

22. በሌላም በኩል በአመልካች የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የስራ ክርክርን ብቻ የሚመለከት ሲሆን ቤተክርስቲያኗ ከቅዱስ ሲኖዶስ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ከላይ ወደታች ያላትን መዋቅር፤ በቅዱስ ሲኖዶሱ የሚተላለፉ መመሪያዎች እና ውሳኔዎች በቤተክርስቲያኗ ሥር ባሉ ገዳማት፣ አድባራት እና አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የሚኖረውን ተፈጻሚነት የሚመለከት አይደለም። በተያዘው የስራ ክርክር ጉዳይ ላይ የመንግስት አንዱ አካል በሆነው ፍርድ ቤት ክርክሩ ታይቶ ሲወሰን የአሰሪና ሰራተኛ ህጉና የግራቀኙ የስራ ውል ግንኙነት ታይቶ ውሳኔ ከሚሰጥ በቀር ህገ ቤተክርስቲያን ተተርጉሞ የሚወሰንበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩ ተጠሪዎች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል።

23. በመሆኑም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ መሠረቱ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ ጉዳዩን ተቀብሎ ለማየት ስልጣን ያለዉ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139 (1) መሠረት የሥራ ክርክር ችሎት ነው፤ አመልካች በክሳቸው በሲኖዶስ ተሰጠ የተባለውን ውሳኔ ጠቅሰዋል መባሉም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ እንዳይወስን የሚከለክል አይደለም፤ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ተቀብለው ለመመልከት እና ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን አላቸው ብለናል።

24. ጉዳዩን ከዚህ አንፃር አይቶ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ አከራክሮ መወሰን ሲገባ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ስልጣን የለኝም በማለት ያሳለፈው ብይን እና ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በመሰረዝ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

25. የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 234706 ጥቅምት 5/2016 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ "በሲኖዶስ ትዕዛዝ መሰረት እንደ ተጠሪዎች ያሉ አካላት ካልፈጸሙ ባላቸዉ አሠራር መሰረት በአስተዳደር ረገድ እንዲፈጽሙ ከሚደረግ በቀር ተጠሪዎች በፍርድ ተገደዉ ውዝፍ ክፍያ እንዲፈጽሙ፣ ..... የሚወሰንበት አግባብ የለም፤ የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ መሰረት አድርገው በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 9(1) እና 231(1/ለ) መሰረት መዝገቡን መዝጋት አለባቸው" በማለት የሰጠው ትርጉም በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ ማግኘት ህገመንግስታዊ መብት ስለመሆኑ የሚደነግገውን የኢ.ፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1)፤ በቀጥታ ወይም በግልጽ ካልታገዱ በቀር ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ክስ ተቀብለው ለማከራከር ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ የሚደነግገውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 4 ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ተቀብሎ ለማየት እና ለመወሰን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 139(1) ስር የተሰጠውን የዳኝነት ሥልጣን፤ እንዲሁም የሃይማኖት ድርጅቶች በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 342/2007 ድንጋጌዎችን እና ከፍሲለል የተጠቀሱ የሰበር ውሳኔዎችን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የተሰጠው ትርጉም ሊለወጥ ይገባል ብለናል።

26. በመሆኑም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26 መሰረት ቀደም ሲል በዚህ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 234706 እና ይህን ተከትለው በተወሰኑ ሌሎች ተመሳሳይ መዛግብት ተሰጥቶ የነበረውን ትርጉም ለውጠናል። ይኸውም ፡- የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011

አንቀጽ 139(1) 'ን መሰረት በማድረግ በሐይማኖት ድርጅቶች ውስጥ አስተዳደራዊ ተግባርን ለማከናወን በተሰማሩ ሰራተኞች የሚነሱ የስራ ክርክሮችን በተመለከተ ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክሩን ተቀብለው አከራክረው ለመወሰን ህጋዊ የዳኝነት ስልጣን አላቸው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ጠ/ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 234706 ጥቅምት 5/2016 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ "በሲኖዶስ ትዕዛዝ መሰረት እንደ ተጠሪዎች ያሉ አካላት ካልተፈጸሙ ባላቸዉ አሠራር መሰረት በአስተዳደር ረገድ እንዲፈጽሙ ከሚደረግ በቀር ተጠሪዎች በፍርድ ተገደዉ ውዝፍ ክፍያ እንዲፈጽሙ፣ ..... የሚወሰንበት አግባብ የለም፤ የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ መሰረት አድርገው በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 9(1) እና 231(1/ለ) መሰረት መዝገቡን መዝጋት አለባቸው" በማለት የሰጠው ትርጉም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26 መሰረት ተለውጧል፡፡
2. በሐይማኖት ድርጅቶች ውስጥ አስተዳደራዊ ተግባርን ለማከናወን በተሰማሩ ሰራተኞች የሚነሱ የስራ ክርክሮችን በተመለከተ ፍርድ ቤቶች የስራ ክርክሩን ተቀብለው አከራክረው ለመወሰን ህጋዊ የዳኝነት ስልጣን አላቸው ተብሎ ተተርጉሟል፡፡
3. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 245930 ሚያዚያ 28/2016 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03000535 ሰኔ 4/2016 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
4. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን የኮ/መ/ቁጥር 245930 በማንቀሳቀስ ከፍሲል የተሰጠውን ትርጉም መሰረት በማድረግ በመዝገቡ የተያዘውን ቀሪ ክርክር መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኝ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡